# ደንብ IKA-RA፣ የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ
# ዘወትር የሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs)
### 2025-2026 የትምህርት ዓመት

**ማውጫ**


ዓላማ እና አጠቃላይ እይታ
ስለ ውጤት አሰጣጥ ስሌት
የቤት ሥራ እና ሠርቶ የማቅረብ ኃላፊነት
የዲስትሪክት ግምገማዎች እና ምዘናዎች
ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ማህበረሰቦች
ግንኙነት እና ተደራሽነት
ስለ ውሂብ/ዳታ መሰብሰብ እና ትግበራ


## ዓላማ እና አጠቃላይ እይታ

**ጥ/Q፡ የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና የሪፖርት ማቅረቢያ ደንቡ ክለሳ የሚደረገው ለምንድነው?**

መ/A፡ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምዘና እና ሪፖርት የማድረግ ልምዶቹን የሚያዘምነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው:-

- ውጤቶችን ከተግባራዊ ይዘት ደረጃዎች ጋር ለማሣለጥ
- የተማሪዎችን አፈጻጸም የበለጠ ግልጽ በሆነ መንገድ ለማሳወቅ
- የተማሪዎችን የመማር እና በትምህርት ላይ የመገኘት ሃላፊነት ለማጎልበት
- የትምህርት ቤቶችን የውጤት አሰጣጥ መለዋወጥ ለመቀነስ

**ጥ/Q፡ እነዚህ የትምህርት ውጤት አሰጣጥ ለውጦች በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ?**

መ/A: አዎ 2025–2026 የትምህርት አመት ጀምሮ 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በሙሉ የዘመነውን የትምህርት ውጤት አሰጣጥ ደንብ ይከተላሉ።

**ጥ/Q፡ እነዚህ ለውጦች ወደ ኋላ ተመልሰው የሚተገበሩ ናቸው?**

መ/A፡- አይደለም እነዚህ ለውጦች ተፈጻሚ የሚሆኑት ከ 2025-2026 የትምህርት አመት ጀምሮ ሲሆን ያለፉትን ዓመታት ውጤቶች አይነኩም።

**ጥ/Q፡ ደንቡን ከየት አግኝቼ ለማንበብ እችላለሁ?**

መ/A፡ የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ ደንቡ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። ደንቡን ለማንበብ እዚህ ጠቅ ያድርጉ

## የትምህርት ውጤት አሰጣጥ ስሌት

### ጥ/Q: የመጨረሻ ውጤቶች ስሌት የሚደረገው እንዴት ነው?

መ/A: የመጨረሻ ውጤቶች ስሌት የሚደረገው በቁጥር የተሰጡ ማርክ ውጤቶች አማካኝ ውጤት ላይ ተመሥርቶ ነው፦

- **የሴሚስተር ኮርሶች:**የሴሚስተር ውጤት የሚሰላው የሁለቱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤቶች አማካይ ነው። (MP1 + MP2) ÷ 2 = የሴሚስተር ውጤት
- **አመታዊ ኮርሶች:** ሁሉንም አራቱን የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤቶችን መደመር እና ለ 4 ማካፈል (MP1 + MP2 + MP3 + MP4) ÷ 4 = የዓመቱ የኮርስ ውጤት

### ጥ/Q: የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጤና እና የአካል ማጎልመሻ ውጤቶች የሚሰሉት እንዴት ነው?

**መ/A:** ልክ እንደቀደሙት ዓመታት፣ እያንዳንዱ የሩብ አመት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ራሱን የቻለ ኮርስ ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህ፣ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ መጨረሻ ላይ የመጨረሻ ውጤት ያገኛሉ። ለመጨረሻ ውጤት የኮርሶች አማካይ ውጤት አንድ ላይ አይሰላም።

### ጥ/Q: የጎደሉ ውጤቶችስ እንዴት ይሰላሉ?

**መ/A:**

- **የተጓደሉ ውጤቶች – የሴሚስተር ኮርሶች፦**

  አንድ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ውጤት ከተጓደለ፣ መምህሩ በመጨረሻ ውጤቱን ካላስተካከለው በስተቀር የመጨረሻው ውጤት M (**የተጓደለ**) ሆኖ ይታያል።

- **የተጓደሉ ውጤቶች – የሙሉ ዓመት ኮርሶች**

  ከአራቱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤቶች አንዱ ባይኖር፣ የመጨረሻው ውጤት በቀረቡት ሦስት ውጤቶች አማካኝ ውጤት ላይ የተመሰረተ ይሆናል። (MP1 + MP2 + MP3) ÷ 3 = የመጨረሻ ውጤት

  ከአንድ በላይ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤት ከሌለ፣ የመጨረሻው ውጤት M (ውጤት የለም) ተብሎ ይመዘገባል።

### ጥ/Q: የማርክ መስጫ ወቅት እና የመጨረሻ ውጤቶች ሁለቱም በሪፖርት ካርዱ ላይ ይመዘገባሉ?

**መ/A:** አዎ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሪፖርት ካርዶች ላይ የሚታየው

- ለእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ በመቶኛ እና በፊደላት ውጤቶች ይመዘገባሉ
- ለእያንዳንዱ ሴሚስተር ወይም አመታዊ ኮርስ የመጨረሻ ውጤት በፊደል (በመቶኛ ሳይሆን በፊደል)

### ጥ/Q፡ የመጨረሻ ውጤቶች በማዋሃድ ይጠጋጋሉ?

መ/A፡ አዎ፣ የመጨረሻዎቹን የፊደል ውጤቶች የማጠጋጋት ማዋሃድ ስሌት ቀርቷል።

### ጥ/Q፡ ተማሪ ለአንድ የማርክ መስጫ ጊዜ NG (No Grade) ካገኘ(ች)፣ የመጨረሻው ውጤት እንዴት ይሰላል?

መ/A፡ ለዓመት የሚቆዩ ኮርሶች፣ የመጨረሻው ውጤት የሚሠላው በቀሪዎቹ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜዎች ላይ የተመሰረተ ነው (ለምሳሌ፡- ለ 4 ከማካፈል ይልቅ ለ 3 ይካፈላል)። ለሴሚስተር ኮርሶች፣ የመጨረሻው ውጤት እንዳልተሟላ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል። መምህሩ(ሯ) የአንድ ጊዜ ውጤት የመጨረሻ መሆኑን ካቀረበ(ች) ያልቀረበው ውጤት እንደሌለ ተደርጎ ይሰላል።

---

## የቤት ሥራ እና ተጠያቂነት

### ጥ/Q፡ አንድ ተማሪ የቤት ሥራ ሠርቶ(ታ) ካልመለሰ(ች) ምን ይደረጋል?

መ/A፡ በውጤት መዝገብ ላይ “Z” ይመዘገባል፣ ይህ ማለት የቤት ስራው ተሟልቶ እንዳልቀረበ የሚያመለክት ሲሆን አሁንም የቤት ሥራው ከተጠናቀቀ ሊቀርብ ይችላል። ተማሪው(ዋ) ድጋፍ ከተሰጠም በኋላ ስራውን በመጨረሻው ቀን ካላጠናቀቀ(ች)፣ መምህሩ “Z” ወደ ዜሮ ይለውጠዋል/ትለውጣለች።

### ጥ/Q፡ ለምዘናዎቹ ዝቅተኛ ውጤት ይኖራል?

መ/A: አዎ ደንቡ ላይ የተደነገገው "የተማሪው ስራ የሚገመተውን ደረጃዎች ለማግኘት ማሻሻል ካሳየ(ች) መምህራን ከ 50 በመቶ በታች የሆነ ውጤት መስጠት የለባቸውም" ይላል። ተማሪው(ዋ) በተመደበው ቀነ ገደብ ስራውን ለማጠናቀቅ ምንም አይነት ሙከራ ካላደረገ(ች) ዜሮ ይሰጣል። ተማሪው(ዋ) በአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት ላይ ከተሳተፈ(ች) ዜሮ ሊመዘገብ ይችላል። (IKA-RA, pg. 11)

### ጥ/Q፡- ተማሪ እየተገመገሙ ያሉትን መመዘኛዎች ማሻሻል የሚያሳይ ማስረጃ እንዴት ይታወቃል?

መ/A፡ ስራው(ዋ) መሰረታዊ መስፈርቶችን ለማሟላት እና ለትምህርት ግቡ የሚያደርገውን/የምታደርገውን እንቅስቃሴ የሚያረጋግጥ እውነተኛ ሙከራ ማሳየት አለበት። ይህ ማለት ስራው(ዋ) ባዶ አለመሆኑን ወይም የዘፈቀደ መልሶች አለመሆናቸውን ማሳየት አለበት ማለት ነው። የተማሪው(ዋ) ስራ በትምህርት ይዘቱ እየተሳተፈ(ች) እና ትምህርቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከረ(ች) መሆኑን ማሳየት አለበት።

### መሰረታዊ መስፈርቶችን ለማሟላት እና ወደ ትምህርት ግቡ ማሻሻሉ(ሏ)ን ለማሳየት እውነተኛ የሙከራ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በቤት ሥራው ላይ ብዙ ጥያቄዎችን በተገቢ ሁኔታ ለመመለስ ጥረት ማድረግ እና ሀሳቡን መረዳት
- ጥያቄውን የሚመለከት እና የይዘት ግለጫ ቃላትን በመጠቀም ያልተሟላ ቢሆንም በከፊል መልስ መጻፍ።
- በሂሳብ ሥራ የመጨረሻው መልስ ትክክል ባይሆንም እንኳ የስሌት ቅደምተከተል ደረጃዎችን ማሳየት።
- ክለሳ ማድረግ የሚያስፈልግ ቢሆንም ከሥራው ጋር የሚጣጣሙ አወቃቀሮችን እና ሃሳቦችን የያዘ ረቂቅ ማቅረብ።
- መመሪያዎችን በመከተል እና ቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦችን በማሳየት ላብራቶሪ፣ ፕሮጀክት፣ ወይም የአፈጻጸም ተግባር መሞከር።

ግቡ ተማሪው(ዋ) መስፈርቱ ለማሟላት በንቃት እየሰራ(ች) መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

**ጥ/Q፡ 50% ድንጋጌ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል?**

መ/A: አዎ ዝቅተኛው 50% መስፈርት በሁሉም የትምህርት ዘርፎች (ሁሉም ተግባራት እና መልመጃዎች/ዝግጅት) ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በመልመጃዎች/በዝግጅት መድብ ላይ መምህራን ከስራው ትክክለኛነት ይልቅ ለማጠናቀቅ በተደረገው ጥረት ውጤት መስጠት ይችላሉ።

**ጥ/Q: የትኞቹ ተግባራት እንደገና መገምገም እንዳለባቸው የሚወስነው ማነው?**

መ/A፡ መምህራን የትኞቹ ስራዎች እንደገና መገምገም እንዳለባቸው ይወስናሉ፤ እና እነዚህን ስራዎች በውጤት መዝገብ ላይ "R" ይጽፋሉ።

**ጥ/Q፡ በአንድ የማርክ መስጫ ወቅት የተገኘ ዝቅተኛ የትምህርት ውጤት ተማሪው(ዋ) በሴሚስተሩ እንዲወድቅ/እንድትወድቅ ሊያደርግ ይችላል?**

መ/A፡ የመጨረሻው ሴሚስተር ውጤቶች በአማካኝ ውጤቶች ላይ ተመስርቶ የተሰሉ ናቸው። በጣም ዝቅተኛ ውጤት በአጠቃላይ አማካይ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ቢችልም፣ ተማሪዎች በሴሚስተሩ ውስጥ የተማሩትን እውቀት ለማሳየት ብዙ እድሎች አሏቸው። አንድ ተማሪ በሴሚስተሩ ካላለፈ(ች)፣ በትምህርት አቅጣጫው ላይ እንዲቀጥል/እንድትቀጥል ለማገዝ የክሬዲት ማግኛ አማራጮች አሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በአንድ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ብቻ የወደቁ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከርእሰመምህሩ እና ከተገቢው ተወካይ ፈቃድ በማግኘት የክሬዲት ማስተካከያ ለመውሰድ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ድጋፎች የተቀመጡት ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ እና የትምህርት ተግዳሮቶችን በወቅቱ እየፈቱ ክሬዲት እንዲያገኙ ለመርዳት ነው። (ክሬዲት ስለማስተካከል IKA-RA፣pg. ይመልከቱ። 15)

**ጥ/Q፡ በአንድ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የሚሰጠው ዝቅተኛ የቤት ሥራ ብዛት ምን ያህል ነው?**

መ/A: እያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- ቢያንስ **9 ሁሉም ተግባራት** የቤት ሥራዎች (ለምሳሌ፡- ፈተናዎች/ቴስት፣ፕሮጀክቶች፣ ድርሰቶች)
- ቢያንስ **5 መልመጃዎች/ዝግጅት** የቤት ስራዎች (ለምሳሌ፡- የቤት ስራ፣ የክፍል ውስጥ መልመጃዎች)

**ጥ/Q፡- ያለፍቃድ መቅረት ቢኖር ያመለጠውን የትምህርት ሥራ ማካካስ ይቻላል?**

መ/A: አዎ ተማሪዎች ከት/ቤት የመቅረታቸው ምክንያት ምንም ይሁን ምን ያመለጧቸውን ስራዎች እንዲሰሩ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

**ጥ/Q፡ አንድ አስተማሪ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ የቤት ሥራ ውጤት ካልሰጠ(ች) ምን ይሆናል?**

መ/A፡ የውጤት አሰጣጥ ደንቡ ላይ ተማሪዎች መማራቸውን እና ማሻሻል የሚያስፈልጋቸውን የሚገልፅ ግብረመልስ እንዲያገኙ ለማድረግ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ የቤት ሥራ ውጤታቸውን ማግኘት የሚጠበቅበት ሁኔታ ተቀምጧል። የመጀመሪያ የማስተካከያ ጊዜ እንዳለ ብንገነዘብም፣ MCPS ከፍተኛ የአሠራር ጥራት ደረጃ ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነው። በዚያ ክፍት ጊዜ ውስጥ አንድ ውጤት ካልተመዘገበ/ካልተሰጠ፣ መምህራን ውጤት ሳይሰጥ የዘገየበትን ምክንያት ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦች ጋር መነጋገር ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከተማሪዎች እና ከሰራተኞች ግብረመልስ ለመሰብሰብ እና በትምህርት ክፍል ውስጥ ወጥነት ያለው ትግበራን ለማረጋገጥ ግልፅ የሆነ የግንኙነት መንገዶችን

ይመሰርታል።

---

## የዲስትሪክት ግምገማዎች እና አጫጭር ፈተናዎች/ቴስቶች

### ጥ/Q፡ ዲስትሪክት አቀፍ ማጠቃለያ ግምገማዎች የሚያስፈልጉት ለምን አይነት ኮርሶች ነው?

መ/A፡ ለሚከተሉት ኮርሶች የዲስትሪክት አቀፍ ማጠቃለያ ግምገማዎች ያስፈልጋሉ፦ (የክፍል-ደረጃ እና አካር) ENG 6-8፣ ENG 9/ ENG 9 for EMLs፣ ENG 10/ ENG 10 for EMLs፣ ENG 11፣ ENG 12፣ Algebra 1 A/B፣ Algebra 2 A/B፣ Pre-Calculus A/B፣ MP 2 እና MP 4 ውጤት የማጠቃለያ ግምገማ 10% ይቆጠራል። በየሩብ ዓመቱ የዲስትሪክት ግምገማ MP ውጤት 10% ይቆጠራል።

### ጥ/Q፡ የዲስትሪክት ምዘናዎች እና የማጠናቀቂያ (EOC) ፈተናዎች ውጤቶች ስሌት የሚደረገው እንዴት ነው?

መ/A:

- **የዲስትሪክት ማጠቃለያ ምዘናዎች፡** የማርክ መስጫ ወቅት 3 እና የማርክ መስጫ ወቅት 4 ውጤቶችን እስከ 10% ይወሰዳል
- **በስቴት የተደነገጉ EOC ፈተናዎች (ባዮሎጂ እና ስነመንግስት)**፡ የሴሚስተር B የማጠቃለያ ውጤት 20% ይቆጠራል

### ጥ/Q፡- በየሩብ ዓመቱ የዲስትሪክት ምዘና እና የሴሚስተር ማጠቃለያ ግምገማ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መ/A፡ የሩብ ዓመት የዲስትሪክት ምዘናዎች በአንድ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የተማሪን የትምህርት ችሎታ ግስጋሴ ለመለካት የተነደፉ ናቸው፤ እና የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤቱ 10% ያልበለጠ ሊቆጠር ይችላል።

የሴሚስተር ማጠቃለያ ግምገማዎች በሴሚስተር መጨረሻ ላይ ይከናወናሉ (የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ 2 እና 4) እና በመላው ሴሚስተር ውስጥ የተማሪን የትምህርት ችሎታ መለኪያ ይሆናል። 2025–2026 የትምህርት አመት፣ የሴሚስተር ማጠቃለያ ምዘናዎች እንዲሁ ከማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤት 10% ይመዘናሉ።

---

## የተለዩ ማህበረሰቦች

### ጥ/Q፡ ተለዋጭ ትምህርት (ALO) ለሚከታተሉ ተማሪዎችስ ለውጦች አሉ?

**መ/A፡** ተለዋጭ ትምህርት ለሚከታተሉ ተማሪዎች ደንቡ ላይ ምንም ለውጦች አልተደረጉም። ሁሉም ተማሪዎች መጀመሪያ ላይ እንደ ዲፕሎማ ተማሪ ስለሚቆጠሩ በዚህ መሰረት ውጤታቸው ይመዘናል። በግለሰብ ሁኔታ ተሞርኩዞ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ተማሪ ከስርአተ ትምህርቱ ጋር በተጣጣሙ ተለዋጭ የትምህርት ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ ማስተማር፣ ምዘና መስጠት፣እና ውጤት በመስጠት ተማሪው(ዋ) የማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ለማግኘት ይሰራል/ትሠራለች። ይህ ለእያንዳንዱ ተማሪ ከግል የትምህርት ፍላጎት፣ ዝንባሌ እና ግብ ጋር የተጣጣመ ትምህርት እና ምዘና መደረጉን ያረጋግጣል።

### ጥ/Q፡ IEP ወይም 504 ፕላን ያላቸው ተማሪዎች የተራዘመ የጊዜ ገደብ ይሰጣቸዋል?

**መ/A፡** አዎ IEP ወይም 504 ፕላን ያላቸው ተማሪዎች የተራዘመ አኮሞዴሽን ጊዜ፣ እንደሁኔታቸው የተስተካከለ የማብቂያ ቀናት **እና** የግዜ ገደቦችን ከግል እቅዶቻቸው ጋር በተጣጣመ መልኩ ይሰጣቸዋል። የተማሪዎችን ስኬት እና ፍትሃዊ የመማር

እድል ለመደገፍ መምህራን ሁሉንም አኮሞዴሽኖችን ማክበር እና መተግበር ይጠበቅባቸዋል።

## ግንኙነት/ኮሙኒኬሽን እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት መድረስ

### ጥ/Q፡ አስተማሪዎች ዜሮ ወይም 50% ከመመዝገባቸው በፊት ተንከባካቢዎችን ማነጋገር ይጠበቅባቸዋል?

**መ/A፡** ዜሮ ወይም 50% ከመመዝገባቸው በፊት ከተንከባካቢዎች ጋር ቀጥታ ግንኙነት ማድረግ ባይጠበቅባቸውም፣ የተማሪ ትምህርት ደጋፊ እና ተባባሪ አካል መሆናቸው በጣም ይበረታታል። በደንቡ መሰረት መምህራን ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ስለተጓደሉ ስራዎች ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመገናኘት እና በማሳወቅ የመመዝገብ ሃላፊነት አለባቸው (IKA-RA,pg. 10)

በተጨማሪም፣ ዜሮ ከመመዝገባቸው በፊት፣ መምህራን ለተማሪ የሚሰጡትን ድጋፍ እና/ወይም ጣልቃ ገብነት በጽሑፍ በመመዝገብ ማሳወቅ አለባቸው። (IKA-RA, pg. 11) እነዚህ ጥረቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ የሚደረግ ድጋፍ
- እንደገና ማስተማር እና ዳግመኛ ግምገማ ማድረግ (አስፈላጊ ከሆነ)
- ከተማሪ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም አማካሪ/ካውንስለር ጋር መገናኘት
- ቀደም ብሎ የተደረጉ ጥረቶች ካልተሳኩ፣ ከትምህርት ቤት አስተዳደር ጋር ግንኙነት ማድረግ

ይህ ሂደት ተማሪዎች ቋሚ ውጤት ከመመዝገቡ በፊት በትምህርቱ ላይ እንዲሳተፉ እና የሚፈልጉትን ድጋፍ እንዲያገኙ እያንዳንዱ እድል መሰጠቱን ያረጋግጣል።

### ጥ/Q፡ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ስለ ለውጦቹ እንዴት ይገለጽላቸዋል?

መ/A፡ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትራንስክሪፕቶች ስለ ውጤት አሰጣጥ እና የተደረጉ ለውጦችን ሪፖርት ለማድረግ፣ ለኮሌጅ መግቢያ እና ለስኮላርሺፕ ግምገማ ሂደቶች ግልፅነትን የሚያረጋግጥ መግለጫ አላቸው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መግለጫ ላይ በውጤት አሰጣጥ ስሌት ላይ የተደረገውን ለውጥ የሚያብራራ መረጃም ይኖረዋል።

## መረጃ መሰብሰብ እና ትግበራ

### ጥ/Q፡ MCPS የተሻሻለውን የውጤት አሰጣጥ ደንብ ትግበራ እንዴት ይቆጣጠራል?

መ/A፡ የውጤት አሰጣጥ አዝማሚያዎችንና ደርዞችን ለመለየት እና ተከታታይነት እና ወጥነት ያለው ትግበራን ለማረጋገጥ MCPS የአጭር ጊዜ እና የመካከለኛ ጊዜ የካርድ ውጤቶችን ጭምር የተማሪዎችን መረጃ በየጊዜው ይመረምራል። በተጨማሪም የተማሪዎችን ተሳትፎ እና የትምህርት ውጤቶችን ለመከታተል በትምህርታቸው ላይ የመገኘት፣ የመከታተል እና የማጠቃለያ ምዘና መረጃዎችን በሁለተኛው እና በአራተኛው የማርክ መስጫ ወቅቶች መጨረሻ ላይ ግምገማ ይደረጋል።